# የብሄራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል

## የምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር  አሰራር መመሪያ

**565/2013**

ጥቅምት 2007 ዓ/ም

ብሄራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ
ምርምር ካውንስል
አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

ሃገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የምታደርገውን መዋቅራዊ ሽግግር በተሟላ መልኩ ለመፈፀምና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት እጅግ ወሳኝና መሰረታዊ ነው፡፡ከዚህ አንፃር ቴክኖሎጂዎችን የመማር፣ የማስገባት፣ የማላመድና የመጠቀም እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የተጠናከረ የምርምር ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ በሃገራችን ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም የምርምር ስራ የሃገሪቱን ዋና ዋና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚፈታ፣ ለሃገራችን የልማት ግቦች መሳካት አስተዋፅዖ የሚያደርግና የቴክኖሎጂ ፍላጎትን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም በተበታታነ መልኩ እየተካሄዱ ያሉና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚፈስባቸው የምርምር ስራዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲመሩና አላስፈላጊ ድግግሞሽና የሃብት ብክነትንም ለማስቀረት፣ ብሎም የሀገሪቱን የምርምር አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት፣ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣትና ይህንኑ በበላይነት የሚከታተልና የሚያስፈፅም ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል ማቋቋም ተገቢ ይሆናል፡፡

የኢፌዲሪ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር **691/2003** ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከተሰጡት ተግባርና ሃላፊነቶች መካከል አንዱ በአንቀጽ **22(10)** የተመለከተው የምርምር ስራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችን ያቋቁማል ፣ ያስተባብራል ፣ ይደግፋል በሚል የተሰጠው ስልጣን ነው፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል ለማቋቋም የሚያግዝ ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ ለብሄራዊ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ቀርቦ የምክር ቤቱን ይሁንታ አግኝቷል፡፡ ይህንኑ የብሔራዊ ሳይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ይሁንታን በመጠቀም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የብሄራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ካውንስል የማቋቋሚያና የአሰራር መመሪያ አወጥቷል፡፡

በፀደቀው መመሪያ መሰረት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሰብሳቢነት ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ከከፍተኛ ትምህርት ኮንሰርቲየም፣ ከግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከሳይንስ አካዳሚ፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ እንዲሁም ከንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተውጣጡ ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች አባል የሆኑበት ካውንስል ተቋቁሟል፡፡ ካውንስሉ ከተቋቋመ በኋላ የራሱን የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ የውስጥ መመሪያ ያወጣ ሲሆን የዝግጅት ምዕራፍን የያዘ የእራሱን የ**2006** በጀት ዓመት ቀሪ ወራት ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በዕቅዱ መሰረትም



ቴ-ሆስፒኒስ
ጋዝብሔ

በ2007 በጀት ዓመት በምርምር ድጋፍ ዙሪያ ለሚሰራቸው ስራዎች የበጀት ዝግጅት አድርጎ ጥያቄውን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በኩል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሰረት ለካውንስሉ የምርምር ድጋፍ ከመንግስት የሚመደበውን በጀት በካውንስሉ ውሳኔ መሰረት የመንግስት የፋይናንስ ደንብ እና መመሪያን ተከትሎ ለመጠቀም እንዲቻል ከካውንስሉ የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ የውስጥ መመሪያ በተጨማሪ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ይህ የምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2.የመመሪያው አስፈላጊነት

1. ካውንስሉ በሚያደርጋቸው የምርምር ድጋፎች ላይ ለተመራማሪዎች የሚሰጠው የድጋፍ ገንዘብ አለቃቀቅና አጠቃቀም እንዲሁም የምርምር በጀት ክትትል ወጥነት ያለው የግልፅነትና ተጠያቂነት አሰራር እንዲኖር ለማድረግ፤

2. ካውንስሉ የሚደግፋቸውን ምርምር ፕሮፖዛሎች የሚገመግሙ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት እንደዚሁም የቴክኒክ ኮሚቴ አባላትን በፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ በሙያቸው ለመደገፍ በአስረጂነት የሚመጡ ባለሙያዎች ለዚሁ ስራ ሲሰማሩ ሊከፈላቸው የሚገባውን የአበል መጠን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

3. አጠቃላይ በምርምር ካውንስሉ አማካኝነት ለምርምር ድጋፍ ከመንግስት የሚፈቀደው የምርምር በጀት አስተዳደርና አያያዝ የመንግስት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ፤ ናቸው፡፡

## ክፍል - አንድ

## ጠቅላላ

### 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ካውንስል የምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ቁጥር **565/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 4.ትርጓሜ

የብሄራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ ላይ የተመለከቱት የቃላት ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 5. የምርምር ድጋፉ ዓላማ

ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች በሌሎች ሴክተሮች ሊደገፉ የማይችሉ ሴክተር ዘለል (cross sectorial) ያላቸውንና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውም ከፍተኛ የሆኑ ትላልቅ ሴክተር ዘለል(cross sectorial) የምርምር ፕሮጀክቶ ፕሮፖዛሎች በውድድር ላይ በተመሰረተ አግባብ ለመደገፍ ነው፡፡

## ክፍል-ሁለት

### ስለ ምርምር ድጋፍ በጀት ዝግጅት አጠቃቀምና አስተዳደር

### 6. ስለ ምርምር ድጋፍ በጀት ዝግጅት

1. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ካውንስሉን በመወከል ካውንስሉ ለሚያደርጋቸው የምርምር ድጋፎች የሚውለውን በጀት እና ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አበልና ለሌሎች ተያያዥ አስተዳደራዊ ስራዎች የሚያስፈልገውን የበጀት ጥያቄ የዓመቱን የበጀት ዑደት ተከትሎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመጠየቅ ያስፈቅዳል፡፡
2. ተፈቅዶ የመጣውን በጀትም በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት በመደልደል ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## 7. ስለ ምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር

1. ለምርምር ድጋፍ ከመንግስት የተመደበው በጀት ካውንስሉ በሚሰጠው አቅጣጫና ውሳኔ አግባብ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 መሰረት ለምርምር ድጋፍ እንዲውል ይደረጋል፡፡

2. በአጠቃለይ በየዓመቱ ካውንስሉ ለሚሰጠው የምርምር ድጋፍ እንዲውል ከሚመደበው በጀት ውስጥ ከ90- 95% (90-95 በመቶ) በቀጥታ ለምርምር ድጋፍ የሚውል ሲሆን ቀሪው እስከ 10% (እስከ 10 በመቶ) የሚሆነው ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አበልና ለሌሎች ተያያዥ አስተዳደራዊ ስራዎች ወጪ የሚውል ይሆናል፡፡

3. ከላይ በአንቀፅ 7/1 ከተመለከተው እስከ 10% (እስከ 10 በመቶ) ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10/1 እና 2 መሰረት ከምርምር ድጋፉ ጋር በተያያዘ ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አበል የሚከፈል ሲሆን፤ ሌሎች ለምርምር ውጤቶች ማዳበሪያ ወርክ ሾፕ ማካሄጃ፤ ካውንስሉ ለመስክ ምልከታ በሚወጣበት ጊዜ ለሚያስፈልጉ አበልና መስተንግዶ ወጪዎች እንደዚሁም ለተያያዥ የህትመትና ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎች የሚያስፈልገው ወጪ ደግሞ በመንግስት የፋይናንስ ደንብ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

4. የሚንስቴር መሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ዳይሬክቶሬትም የፋይናንስ ደንብና መመሪያን ተከትሎ በካውንስሉ ውሳኔ መሰረት የገንዘብ እንቅስቃሴውን ይከታተላል፤ ያስተዳድራል፡፡

5. የገንዘብ አጠቃቀሙ በየዓመቱ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት እየተመረመረ ሪፖርት የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

## 8. ለምርምር ማካሄጃ ስለሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ መጠን

1. ካውንስሉ አወዳድሮ የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን እንደ ፕሮጀክቱ ሃገራዊ ጠቀሜታ፤ ስፋትና ጥበት እየታየ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ለምርምር ድጋፉ የሚሰጠው ከፍተኛ የበጀት ጣሪያም ብር 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን ብር) ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ የገንዘብ ድጋፍ መጠን እንደ ወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም እየታየ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

2. ለምርምሩ የሚውለው የገንዘብ ድጋፍ የሚፈፀመው በካውንስሉ  አሰራር መመሪያ መሰረት ሲሆን አፈፃፀሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

3. የድጋፉ የመጀመሪያው ክፍያ የድጋፉ ስምምነት ፊርማ በተፈረመ በኋላ የሚፈፀም ሆኖ የድጋፉ አከፋፈል መጠን በተመለከተ ለመጀመሪያ ዙር የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን በፕሮጀክቱ ዕድሜ ላይ ተስርቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት ፡-

ሀ/ የፕሮጀክቱ ዕድሜ  እስከ 1 ዓመት ከሆነ ለመጀመሪያ ዙር የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ከጠቅላላው የፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከተፈቀደው በጀት ብር 50 % ይሆናል፡፡ቀሪው የሁለተኛው ዙር  ገንዘብ እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍ ገንዘብ አከፋፈል ተፈፃሚ የሚሆነው ስለ ፕሮጀክቱ ክንውን የሚቀርበውን የቴክኒክ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት በመገምገምና በተጨማሪም በመስክ ተገኝቶ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የደረሰበትን ደረጃ በመመልከት ይሆናል፡፡

ለ/ የፕሮጀክቱ ዕድሜ ከ1 ዓመት በላይ እስከ 2 ዓመት የሚደርስ  ከሆነ ለመጀመሪያ ዙር የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ከጠቅላላው የፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከተፈቀደው በጀት ብር 30 % ይሆናል፡፡ ቀሪው 70 % የድጋፍ ገንዘብ አከፋፈል ተፈፃሚ የሚሆነው ስለ ፕሮጀክቱ ክንውን በመጀመሪያው 6 ወርና በሁለተኛው ስድስት ወር የሚቀርበውን የቴክኒክ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት በመገምገምና እንደአስፈላጊነቱም በመስክ ተገኝቶ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የደረሰበትን ደረጃ በመመልከት ቀሪው ገንዘብ እንደሁኔታው የሚለቀቅ  ይሆናል፡፡

ሐ/ የፕሮጀክቱ ዕድሜ ከ2 ዓመት በላይ እስከ 3 ዓመት የሚደርስ ከሆነ ለመጀመሪያ ዙር የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ከጠቅላላው የፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከተፈቀደው በጀት ብር 30 % ይሆናል፡፡ ቀሪው 75 % የድጋፍ ገንዘብ አከፋፈል ተፈፃሚ የሚሆነው ስለ ፕሮጀክቱ ክንውን በመጀመሪያው 6 ወርና በሁለተኛው ስድስት ወር እና በሶስተኛው 6 ወር የሚቀርበውን የቴክኒክ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት በመገምገምና እንደ አስፈላጊነቱም

በመስክ ተገኝቶ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የደረሰበትን ደረጃ በመመልከት ቀሪው ገንዘብ እንደሁኔታው የሚለቀቅ ይሆናል፡፡

## 9. የድጋፉን ቀሪ ገንዘብ ስለመመለስ

በምርምር ቡድኑ ጥቅም ላይ ያልዋለን ገንዘብ ስለመመለስ በተመለከተ በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ አንቀፅ 16 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 10. ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ስለሚሰጥ የሙያ አበል ክፍያ

1. በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የምርምር ድጋፍ መመሪያ አንቀፅ 9/9.1 ላይ በተመለከተው መሰረት የሚቋቋመው ቴክኒክ ኮሚቴ ለድጋፍ የቀረቡ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎን ለመገምገም፣ የተደገፉ ፕሮጀክቶችን በመስክ ተገኝቶ ያሉበት ደረጃ ለመመልከት እንደዚሁም ካውንስሉ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ለኮሚቴው አባላት የምግብና አልጋ ወጪዎችን በመሸፈን የሙያ/የኪስ ገንዘብ/ የሚከፈለው አበል መጠን በቀን ብር 500 ( አምስት መቶ ብር ) ይሆናል፡፡

2. ቴክኒክ ኮሚቴው ፕሮጀክቶችን በሚገመግምበት ወቅት ከሚገመገመው ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ ባላቸው ሙያና ልምድ በአስረጂነት የሚቀርቡ ባለሙያዎችም በዚሁ መመሪያ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በተቀመጠው አግባብ ይሆናል፡፡

3. ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል በመስክ ተገኝቶ ምልከታ፣ክትትልና ግምገማ ለማድረግ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ የሚደረጉ የአበልና ሌሎች መስተንግዶ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ...
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት
... አበባ

## ክፍል- ሶስት

## የምርምር ፕሮጀክት የፋይናንስ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ

### 11.የፋይናንስ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ

1. በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል አማካኝነት ድጋፍ የሚሰጣቸው የምርምር ፕሮጀክቶች በሙሉ መተግበር ያለባቸው ለድጋፍ ቀርቦ በፀደቀው ዋና ፕሮፖዛልና በተፈረሙ የድጋፍ ስምምነት አንፃር ብቻ ይሆናል፡፡
2. የፕሮጀክቱ ትግበራ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ እየተተገበረ ወይም እየተሰራ መሆኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በቴክኒክ ኮሚቴውና ይህን ስራ እንዲከታተል በተሰየመው የስራ ክፍል አማካኝነት የፋይናንስ አጠቃቀሙ ክትትልና ቁጥጥር ያደረጋል፡፡ የግኝቱ ሪፖርትም ለካውንስሉ ይቀርባል፡፡

### 12. ድጋፍ ስለማቆም ወይም ማቋረጥ

ለምርምር ቡድኑ የሚደረገውን ድጋፍ ስለማቆም ወይም ማቋረጥ በተመለከተ በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ የውስጥ መመሪያ አንቀፅ 22 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል-አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. የህግ ጉዳይ (Legal Issue)

ከምርምር ድጋፉየገንዘብ አጠቃቀም ስምምነት ጋር ተያያዥነት ኖሯቸው የሚነሱ የህግ ጉዳዮች በሃገሪቱ ህግ መሰረት የሚታዩ ይሆናሉ፡፡

### 14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ የምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ካውንስሉ ባመነበት ጊዜ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፡፡

## 15. የድጋፍ መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ የምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ከጥቅምት/ 2007ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ደሚቱ ሃምቢሳ

ሚንስትር

ጥቅምት 2007 ዓ/ም

አዲስ አበባ